# በቃሊቲ ቅናት - -በዓላማ ጽናት

ከድሚልኝ ብዕሬ-ዘአዲሱ ገበያ

ሃገሯን ምድሪቷን
        አድባሯን ቀስቅሰው
ወጣት አዛውንቱን
        ስሜቱን አናውጠው
ተስፋውን ምኞቱን
        ትግሉን አፋፍመው
ፍትህን ሰላምን
        አንድነትን ሰብከው
ክፉ ቀን ሲመጣ
        ከቃሊቲ ዘምተው
ያድራሉ መሪዎች
        በሰላም ተኝተው

ኸረ ተኙ ተኙ
        ፈጣሪ ይርዳችሁ
የቃሊቲ አድባር
        አለሁ ትበላችሁ
አልጋዉም መደቡም
        ትራሱ ይመቻችሁ
ያገራችን ፀሎት
        እንባ ይጠብቃችሁ

ለነፃነት ተስፋ
        ቃብድ ተቀብላችሁ
ያገሩን የሕዝቡን
        ልብ አንጀት በልታችሁ
ምስጢሩ ምን ይሆን
        የግዞት ፍቅራችሁ
የሃገር ፍቅር ዕዳ
        ታላቅ ነው ሥራችሁ

የቃሊቲ ኑሮ
        ስቃዩ መከራው
ዘለፋና ስድቡ
        ዱላና ወከባው
ግዞት መሪር ሕይወት
        ቢበዛም ሰቆቃው
ለናንተ ዕዳችሁ
        ለኛ ቅርሳችን ነው

መታሠር መጋዙን
        እናንተ ስትኖሩት
ለሃገር ለወገን
        መስዋዕት ስትሆኑት
የህሊና ጽናት
        ምሳሌን ስትቸሩት
ወዳጅም ጠላትም
        ግዞትን ተመኙት

ቀኑብሽ ቃሊቲ
        አንቺ ታድለሻል
ምሁሩን መሪውን
        ስብሰባ ጠርተሻል
ዶክተር ጋዜጠኛ
        ዳኛውን ጋብዘሻል
ብሔራዊ ትኩረት
        ስምን አግኝተሻል
ኮንፈረንሱ ይብቃ
        ጩኸት በዝቶብሻል
ታሪክሽ እንዲያምር
        ፍትሓት ይገባሻል

***************************

© ድሚልኝ ብዕሬ-ዘአዲሱ ገበያ
ሰኔ 1999
zeaddisu_gebeya@yahoo.com
June 2007